


# የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት
# SPA SERVICE ENTERPRISE

ዓመታዊ መጽሔት ቁጥር 14
የካቲት 2018 ዓ.ም



# ማውጫ


የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት ........................ 3

የድርጅቱ ስራ አመራር ቦርድ አባላት ........................ 5

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ........................ 6

የድርጅቱ ማኔጅመንት አባላት ........................ 8

የፍ/አገ/ድ/ የስራተኛ ማህበር ሊቀመንበር መልዕክት ........................ 9

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት አመሰራረት በአጭሩ ........................10

ከኢንፎርሜሽን ኮሙ/ቴክኖ/ ዳይሬክቶሬት........................ 13

የ2017 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ........................ 17-23

የድርጅታችን የላውንደሪ አገልግሎት እንደሚሰጥ ያውቃሉ? ........................ 24

የመዝናኛ እና የቁም ነገር አምድ ........................ 27-29

ከፎቶ ማህደር ........................ 32-33

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት የፋይናንስ መረጃ ........................ 34-45

ከፎቶ ማህደር ........................ 47-51

ድርጅቱን አገልግለው ጡረታ የወጡ ሰራተኞች ........................ 55


# የአዘጋጆች መልዕክት

ድርጅታችን በ2017 በጀት ዓመት ያስቀመጣቸውን የሽያጭ እና የትርፍ ዕቅድ ከማሳካት የተለያዩ የማርኬቲንግ እና የቢዝነስ ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም ከፍተኛ የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት ልዩ ልዩ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች በመስራታቸው እንዲሁም በድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ እና ማኔጅመንት በተሰሩ ስትራቴጂክ ጉዳዮች በበጀት ዓመቱ የያዘውን ዕቅድ በተሳካ ሁኔታ መፈፀም ችሏል።

የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ፣ ማኔጅመንት እና ሠራተኛ ማህበሩ ከመላው ሠራተኛ ጋር ከምንግዜውም በተሻለ ሁኔታ ተናቦና ተግባብቶ በመሥራቱ ከዚህ ውጤት መሳካት የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል።

የ2017 በጀት ዓመት የድርጅቱን ሥራ አፈፃፀም አስመልክቶ በተዘጋጀው በዚህ መፅሔት ላይ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ፣ የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ፣ የሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ያስተላለፉትን መልዕክት እና የበጀት ዓመቱን የሥራ አፈፃፀም ፣ ኦዲት የተደረገ የሂሳብ ሪፖርት ፣ ያለፉትን አምስት ዓመታት የትርፍና የሽያጭ እንዲሁም የእንግዳ ቁጥር አፈፃፀም ፣ የድርጅቱን እንቅስቃሴ ገላጭ የሆኑ ፎቶግራፎች ፣ ጠቃሚ መረጃዎችን የያዙ መጣጥፎች እና የተለያዩ መልዕክቶችን የሚያስተላልፉ ግጥሞችን ያካተተ መፅሔት

ከማዘጋጀት ጥረት ተደርጓል።

መልካም ንባብ

አዘጋጅ የገ/ጥ/አገ/ልማ/ኮሚ/
ዳይሬክቶሬ

# የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት

## ራዕይ

በተፈጥሮ ፍልውሃ መታጠቢያ በስፓ እና በሆቴል አገልግሎት ግንባር ቀደምና ተመራጭ ሆኖ ማየት።

## Vision

To be pioneer and favorable in the country's natural Hot spring water bath spa hotel service

## ተልዕኮ

ድርጅቱን በርፈ ብዙ አገልግሎት ማለትም ደረጃውን የጠበቀ የመታጠቢያ፣ የፊዚዮቴራፒ፣ የሳውና ባዝ፣ የስቲም ባዝ፣ ህክምና፣ የሆቴል፣ የመናፈሻ እና የመሰብሰቢያ አዳራሽ አገልግሎቶቻችንን በብቃት በጥራት በመስጠት የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ፍላጎት ማርካት እና የቱሪዝም መዳረሻ እንዲሆን በማስቻል የሃገሪቱን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት የበኩሉን ድርሻ መወጣት ነው ::

## Mission

To contribute its parts in making organization broad standardized services like bath,physiotherapy, steam bath, sauna bath, medium level medical clinic, hotel service, recreation and meeting hall services in efficiency and quality and to satisfy the beneficiaries'need and marke it tourism destination.

## እሴት

የአገልግሎት ጥራትና የመስተንግዶ ቅልጥፍና ተቀዳሚ ተግባራት ናቸው፣
ደንበኞች የህልውናችን መሰረት ናቸው፣
የደንበኞቻችንን አስተያየት መቀበልና ስህተታችንን በማረም ደንበኞችን ማርካት መርሃችን ነው::
በተነሳሽነት ፣ በቁርጠኝነትና በጋራ ስሜት ለውጤት መስራት መርሃችን ነው::
ግልፅነትና ተጠያቂነት፣ታማኝነት መርሃችን ነው::

## Core Values

Customer is our base of existence.
Accepting the customers opinion & suggestion and correct our mistake and satisfy customers.
To work in initiation, commitment and honesty is our principle.
Transparency, accountability and honesty is our principle.
Quality service delivery and service sharing is our priority function.
To deliver service that is based on honesty, quick and saving to our customers service



## ክቡር ሬ/ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ
## የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት

ሀገራችን ሁልጊዜም እንድታድግልን፣ እንድትበለፅግልን፣ እንፈልጋለን ለዚህ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ያለውን የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሳደግ መንግስት ትኩረት ሰጥቶበት ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚና ገፅታ ግንባታ የተሻለ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ጥረት እየተደረገ ነው። ጤናው የተጠበቀ አምራች እና ብሩህ አዕምሮ ያለው አርቆ አሳቢ አገሩን ለበጎ የሚለውጥ ዜጋ በመፍጠር ዘርፉን የበለጠ በማሳደግ ሀገራችንን በአዎንታዊ ጎኑ በሚገባ በማስተዋወቅና በኢኮኖሚውም ላይ ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ትኩረት ተሰጥቶ አያሌ ሥራዎችም በሀገር ደረጃ እየተሰሩ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

የፍልውኃ አገልግሎት ድርጅት ከአገራችን ግንባር ቀደም የጤናና የመዝናኛ ማዕከላት አንዱ ነው። በእምቅ የተፈጥሮ ሃብቱም በእቴጌ ጣይቱ አመልካችነት ለከተማችን በአሁኑ መልክ መቀርቀር መነሻ መሆኑ በታሪክ ደገለባል። ከዚያ ጊዜ አንስቶም የከርሰ ምድር የተፈጥሮ ፍልውሃን በመጠቀም ለህብረተሰብ ጤንነት አስፈላጊ የሆኑትን የመታጠቢያ፣ የመታሻ፣የሳውና ባዝ፣ የእስቲም ባዝ እና በተጓዳኝም የሆቴል አገልግሎቶችን ለሰፊው ሕዝብ በእጅግ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚሰጥ በኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ስር የሚተዳደር ድርጅት ነው ።

ድርጅቱ ተልዕኮውን ከማሳካት አንፃር በየጊዜው የሚያጋጥሙትን ችግሮችን በፅናት በማለፍ የተጠቃሚ እንግዶችን ፍላጎት ለማርካት እና የገበያ አድማሱን በማሳደግ ከፍተኛ ቀጥር ያላቸውን እንግዶችን በማስተናገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እመርታ ያሳየ ድርጅት ለመሆን የበቃ ሲሆን

የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና ለመጨመርም ከምንጊዜውም በተሻለ እየተጋ ያለ ድርጅት ነው::

በተጨማሪም በአሁኑ ሰዓት ድርጅቱ የተገልጋዩን ፍላጎት ለማሟላት በመታና፣ በሳሙና ባዝ፣ በእስቲም ባዝ እንዲሁም በሆቴል የእንግዶችን እርካታ የሚያሳድግ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለመከረት በሂደት ላይ ያለ ሲሆን ይህም የገበያ አድማሱን ከማስፋት እና ሀብቱም ገቢውንም ከማሳደጉም ባሻገር የድርጅቱን ለቅም በማጉልበት ህብረተሰቡ ልዩ ልዩ አማራጮችን እንዲያገኝ ለማድረግ ታስቦ እየተሰራበት ይገኛል::

በአጠቃላይ ድርጅቱ ለከተማው ህብረተሰብ በዋናነት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ወገኖቻችን ፈውስ ሰጪ የሆነ የከርሰ ምድር ፍልውኃ መታጠቢያ፣ የመታና፣ የሳሙና ባዝ እና የእስቲም ባዝ አገልግሎቶችን ለማበርከት ጠቃሚ የሆኑ ግልጋሎቶችን እየሰጠ ያለ ድርጅት ሲሆን በሆቴል አገልግሎትም የረዥም ጊዜ ልምድ ያካበቱ እና በሚያዘጋጃቸው ባህላዊ ምግቦች ተወዳጅነትን ያተረፈ ድርጅት እንደመሆኑ በቀጣይም የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ለማሳደግ እና የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ፍላጎት ለማርካት የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ፣ ማኔጅመንት እና መላው ሠራተኛ እጅና ጓንት በመሆን ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ ጠንክረን እንደምንሰራ በዚህ አጋጣሚ ላረጋግጥ እወዳለሁ።

አመሰግናለሁ

# የድርጅቱ ስራ አመራር ቦርድ አባላት



[illegible]
የፋ/አገልግሎት ድርጅት
የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ



[illegible]
የፋ/አገልግሎት ድርጅት
የሥራ አመራር ቦርድ አባል



ዶ/ር [illegible]
የፋ/አገልግሎት ድርጅት
የሥራ አመራር ቦርድ ም/ሰብሳቢ



አቶ [illegible]
የፋ/አገልግሎት ድርጅት
የሥራ አመራር ቦርድ አባል



ዶ/ር [illegible]
የፋ/ አገልግሎት ድርጅት
የሥራ አመራር ቦርድ አባል



አቶ ኤርሚያስ መኮንን
የፋ/አገልግሎት ድርጅት
የሥራ አመራር ቦርድ አባል



አቶ መስፍን አሸቱ
የፋ/ አገልግሎት ድርጅት
የሥራ አመራር ቦርድ አባል



ወ/ሮ ትዕግስት [illegible]
የፋ/አገልግሎት ድርጅት
የቦርድ ፀሐፊ




# ክብርት ወ/ሮ ታደለች ዳለቾ
# የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር

በተፈጥሮ ፍልውሃ የመጠቀም ጅማሮ በንግስት እቴጌ ጣይቱ በጡል መጀመሩና ለአዲስ አበባ ከተማ መቆርቆር ምክንያት መሆኑን በታሪክ ተመዝግቧል:: በ1897 ዓ.ም. በአጼ ምኒሊክ ዘመን የተጀመረው በፌንፌኒ ሜዳ በተፈጥሮ ፍልውሃ መጠቀም ዘመናትን እየተሻገረ መጥቶ በዘመናዊ መልክ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግስት ፍልውሃ ለተለያዩ በሽታዎች ፈውስ ለጤና ለመዝናና አገልግሎትም ተወዳጅ እየሆነ በመምጣቱ በዘመናዊ መልክ አዲስ ፍልውሃ ሆቴልና የተለያዩ የመታጠቢያ አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች ተሰርተው ሐምሌ 23 ቀን 1956 ዓ.ም. በአጼ ኃይለ ሥላሴ ተመርቀው አገልግሎት መስጠት በመጀመራቸው ድርጅታችን ዘመን ተሻጋሪ የሕዝብ አገልጋይ ድርጅት አድርገውታል:: በተለያዩ ወቅቶችም ድርጅቱ ያደረጋቸው የማስፋፊያ ሥራዎችና አገልግሎት ማሻሻያዎች እያደገ ከመጣው የተጠቃሚ ቁጥር አንፃር አገልግሎቱን ተደረሽ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል::

ድርጅቱ በ2017 በጀት በመታጠቢያ፣በሃይድሮ ቴራፒ/ማሳጅ በሣውና ባዝ፣ በስቲም ባዝና በሆቴል አገልግሎቶች 2,324,848 እንግዳ ለማስተናገድ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን 1,862,784 ተስተናግዶል የእቅዱን 80.12%:: በሽያጭ ገቢ ብር 360,321,552.00 ለማግኘት የዕቅዱን ብር 356,260,983.00 በዕቅድ የተያዘ 98.87% አከናውኗል:: በበጀት አመቱ ብር 80,569,326.00 ትርፍ ከታክስ በፊት ለማግኘት ታቅዶ ብር በማግኘት 82,758,078.00 የእቅዱን 102.72% አሳክቷል።

ለዚህ ከፍተኛ ወጪ የተገኘው የድርጅቱ ስራ አመራር ቦርድ የሚያደርገው ጠንካራ ድጋፍና ክትትል፣የማኔጅመንቱ የጋራ አመራር ሰጪነትና የእለት ተለት የሥራ ክትትል፣ የሠራተኛ ማኀበር አመራር ከድርጅቱ ጋር ባለው ሰላማዊ የስራ ግንኙነትና የመጣው ፈጻሚ ሠራተኛ ትጋት ነው።

የድርጅቱ አገልግሎት የተመሠረተው በፊንፊኔ ሜዳ ከተቆፈሩ ጥልቅ ጉድጓዶች በሚወጣ የከርሰ-ምድር ፍልውሃና ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ከሚመጣ ቀዝቃዛ ውሃ ላይ ሲሆን በከተማው የሚገኘው ቀዝቃዛ ውሃ ድርጅቱ ከሚያስፈልገው የቀዝቃዛ ውሃ መጠን አነስተኛ በመሆኑ በተደጋጋሚ የውሃ እጥረት የሚያጋጥም በመሆኑ ከተገልጋዮች ከፍተኛ ቅሬታ የሚቀርብ ከመሆኑ ባሻገር ለድርጅቱ ገቢም አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ቆይቷል።

ይህንን ችግር ለመፍታት እንዲቻል ድርጅቱ በኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን የውሃና ኢነርጂ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ በድርጅቱ አቅራቢያ የቀዝቃዛ ውሃ ያለበትን ቦታዎች በማስጠናት በጥናቱ መሠረት ከወዳጅነት ፓርክ ደርባ ለጉድጓድ ቁፋሮና ሌሎች ስራዎች የሚሆን መሬት ከሚመለከታቸው አካላት በማስፈቀድ የቀዝቃዛ ውሃ ጉድጓድ በድርጅቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከድርጅቱ ገቢ ውጭ ያስቆፈረው ጉድጓድ መስመር በመዘርጋት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል።

ድርጅቱ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ባለቤትነት ስር የሚተዳደር በመሆኑ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የከርሰ-ምድር የተፈጥሮ ፍልውሃ የጤናና የመዝናኛ /የቱሪዝም/ ፍላጐትን በተሻለ ተወዳዳሪነትና ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ጥናቶች እያካሄደ ስለሆነ ድርጅታችን የተሻለ ተወዳዳሪ እንዲሆን የፍልውሃን ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ አቅሞች/ፖቴንሻል/ ያገናዘበ ኢንቨስትመንት በማካሄድ ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ተገልጋዩች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ወደ መስጠት የሚያሸጋግር ዝግጅት ተጀምሯል።

በመጨረሻም በ2018 በጀት አመትም ሁሉም የድርጅታችን ባለድርሻ አካላት የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ፣ የድርጅቱ ማኔጅመንት፣ መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበርና መላው የድርጅቱ ሰራተኞች በተቀናጀ ሁኔታ በመንቀሳቀስ እቅዳችንን እንደምናሳካ እምነታችን የጸና ሲሆን በአገልግሎታችን የምትጠቀሙ ውድ ተገልጋዮቻችን አገልግሎታችን ለማሻሻል ለምትሰጡን አስተያየቶች አክብሮታችንን እንገልፃለን፡

አመሰግናለሁ።

# የድርጅቱ ማኔጅመንት አባላት



[illegible]
ዋና ዳይሬክተር



አቶ [illegible]
ምክትል ዋና ዳይሬክተር



አቶ [illegible]
የዋና ዳይሬክተር አማካሪ



አቶ [illegible]
[illegible]



ወ/ሮ [illegible]
[illegible]



ወ/ሮ አረጋሽ ጌታቸው
የሰው ኃ/ል/አ/ዳይሬክተር



ወ/ት መሰረት ገብሬ
የበጀትና ፋይናንስ ተ/ዳይሬክተር



ወ/ሮ ኢትዮጵያ አብርሃም
የገ/ጥና/አገ/ልማ/ኦ/ተ/ዳይሬክተር



አቶ ደረጀ ሽፈራው
የግዥና ንብ/አስ/ዳይሬክተር



አቶ ተስፋዬ ሜኔ
የሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክተር



አቶ ፕራይስ አሰፋ
ሆቴል መ/አገ/ዳይሬክተር



አቶ አማኑኤል ታደሰ
የህግ አገ/ዳይሬክተር



አቶ [illegible]
የማታ ሥራ አስኪያጅ



አቶ [illegible]
የውሃ ል/አ/ም/ቴ/ዳይሬክተር



አቶ ተስፋዬ ላቀው
የውስጥ ኦዲት ዳይሬክተር



አቶ [illegible]
ኢስትራቴጂክ ሥ/አ/አ/ዳይሬክተር



# ወ/ሮ ትዕግስት ሽፈራው
# የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት የሰራተኛ ማህበር
# ሊቀመንበር መልዕክት

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ለህብረተሰቡ ዘረፈ ብዙ አገልግሎትን እየሰጠ ያለ ድርጅት መሆኑ ይታወቃል:: ይህም አገልግሎት የሆቴል ፣ የመታሻ ፣ የሻወር ፣ የእስቲም ፣ የካፌ እና የመኝታ የመሳሰሉትን አገልግሎቶችን የተገልጋዩን ፍላጎት ያሟላ እንዲሆን ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በተመጣጣኝ ዋጋ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል ይህም አገልግሎት የተሳለጠ እንዲሆን የፍልውሃ አገልግሎት ማኔጅመንትና ሠራተኞች በጋራ በመጣመር የኢንዱስትሪ ሰላምን በመጠበቅ ከቦርድና ከኢንቨስትመንት ሆልዲንግ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት በዙሪያው እና በድርጅቱ ውስጥ የሚካሔዱ የልማት ሥራዎችንና ድርጅቱን ለማዘመን ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በግንባር ቀደምትነት በመደገፍ ድርጅቱን ወደፊት ለማራመድ በሚደረገው ጥረት ይሁን የሚያስኝ ሲሆን ይህን እንቅስቃሴ ባለበት ሁኔታ የተለያዩ አጣብቂኝ የሆኑ ችግሮች ቢያጋጥምም ሠራተኛው ጠንካራነቱ ከቀድሞም የታወቀ ስለሆነ በዚህ በመቀጠል ከበላይ አካል በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የድርጅታችን ገጽታ በመቀየርና በበለጠ የገቢ ምንጫችን በሚያድግበትና ተጠቃሚነታችን እየጨመረ እንዲሄድ ከወትሮ በበለጠ ከድርጅቱ ጋር ያለውን የኢንዱስትሪ ሠላምና አብሮነት በፍጹም ቅንነትና ቁርጠኝነት በመነሳት ለበለጠ ለውጥ በመስራት ሀገራችንንም ድርጅታችን በተለይ እራሳችን በማብቃት ተጠቃሚ በማድረግ በቀጣይ ለበለጠ ውጤት እንደንደርስ አደራ እላለሁ::

አመሰግናለሁ

# የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት አመሰራረት በአጭሩ

በኢትዮጵያ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የፍልውኃ ምንጮች፣በተለያዩ ክልሎቿ እንደሚገኙ የተረጋገጠ ነው። ከመካከለኛው ምሥራቅ ከሊባኖስ አካባቢ በሚነሳው ታላቁ ስምጥ ሸለቆ ወሰመጥ ላይ ስለምትውል አብዛኛው መልክአ ምድራዊ አካልዋ የፍልውሃ የልዩ ልዩ ጠበሎች የተለያዩ ፍቱን መድኃኒት ያቋቱና ያዘሉ ንጥረ ነገሮች ምንጮች በቀላሉ ሊገኙ የሚያስችሉ ፀጋዎችና አስደናቂ ተፈጥሮአዊ ገጽታዎች እንዳሏት የታወቀ ነው። የአዲስ አበባ ፍልውሃም ከእነዚሁ ሕፍይና ግሩም በረከቶች መካከል አንዱ ነው። በዚህ የተነሳ ህብረተሰብ ለተለያዩ በሽታዎች ማለትም ለመገጣጠሚያ ብግንት፣ ለቁርጥማት፣ ለነርቭ በሽታ፣ ለአጥንት መሟሟት ፣ለጡንቻ መተሳሰርና መሰል የጤና ችግሮች ፈውስ ሰጪ የሆነውን ከከርሰምድር የሚፈልቅ የፍልውሃ ጠበል ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመናዊ መልክ የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅትን እንዲመሰረት አደረጉ።

## የአዲስ አበባ ከተማ አቆራቆር እና የፍልውሃ ቁርኝት

በከተማችን ግማሽ ሚሊዮን ያህል ሕዝብ እንደሚኖር ይገመታል። ይህም ሕዝብ ከሚጠቀምባቸው የኪራይም ሆነ የራስ መኖሪያ ከሆኑት ቤቶች ውስጥ ምን ያህሉ የመታጠቢያ ክፍል አላቸው ? መልሱ የሚጠበቀው ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ነው። ሐምሌ 23 1956 ዓ.ም ተመርቆ የተከፈተው አዲሱ ፍልውሃ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የመታጠቢያ ቤት የሌላቸውን ውስጥ የመታጠቢያ ቤት የሌላቸውን ሰዎች የሚያገለግል ነው።በልዩ ልዩ ደረጃ የተመደበ 140 የመታጠቢያ ክፍል ያለው ይህ ድርጅት 1,820,000 ያህል ወጪ እንደሆነበት ታውቋል።

የሕክምና ሊቃውንት ለጤና አጠባበቅ ይረዳል ብለው ከሚሰጡት ምክር አንዱ የሰውነት ንፅህና መጠበቅ ነው።ንጽሕናችንን የምንጠብቀው ከላይ የምንለብሰውን ልብስ በማፅዳትና በማሳመር ብቻ አይደለም። የገላችን አለመታጠብ የውስጥ ልብሳችንን በቶሎ ሊያሳድፈው ይችላል። የገላችን አለመታጠብ በአካባቢያችን የሚኖሩት ሰዎች የማህበራዊ ኑሮ ደስታ ሊቀንስ ይችላል። የገላችን አለመታጠብ የጤና ጠንቅ ሊያስከትል ይችላል።ገላችንን መታጠብ ፀጉራችንን ማሳጠር ጥርሳችንን መፋቅ ከማህበራዊ ኑሮ ግዴታችን አንዱ ነው።

በአዲስ አበባና በአካባቢው ህዝብ ዘንድም ተፈላጊነቱ እየደገ በመሄዱ ይህንኑ የሕዝቡን ፍላጎት ጊዜው በፈቀደ መጠን ለማርካት እንዲቻል ሁለት ክፍል ያለው መታጠቢያ ቤት በ1954 ዓ.ም ተሰርቶ ሕዝቡ ሲጠቀምበት ቆየ። ከዚያም በኋላ ግርማዊነትዎ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት አልጋ ወራሽ በሆኑ ጊዜ ድርጅቱ ተስፋፍቶ የተሻለ አገልግሎት ለሚወዱት ህዝብዎ እንዲሰጥ በማሰብ አዛዥ ወርቅነህና ሌሎች ባለስልጣኖች ሌሎች ተጨማሪ ክፍሎችንና ተቋም እንዲሰሩ ታዘው አያሌ የመታጠቢያ ክፍሎችን በተሻለ አኳኋን ተሰርተው እስካሁን አገልግሎት ሰጥተዋል።ዘመናዊ መታጠቢያ ለህዝቡ እንዲሰራለት ግርማዊነታቸው በሰጡት መሰረት አስፈላጊው ጥናት በ1954 ዓ.ም ተጠናቆ የዚህ ሕንፃ ስራ በ1954 ዓ.ም ተጀመረ። ስራውም ሁለት አመት ያህል ከፈጀ በኋላ እነሆ በንጉሰ ነገስቱ ተመረቀ። ይህ የፍልውሃ መታጠቢያ ቴድሮስ የተባለ አጤኒ ኩባኒያ እንዲሁም ለስራ ተቋራጭ ለሶሌል ቦኔ ኩባኒያ በተባለ ተገንብቶ ተሰራ።



ግርማዊ ጃንሆይ አዲሱን ፍልውሃ
ምረቃት ስነ ስርዓት
ላይ ሪባን በመቀስ ሲቆርጡ
ሐምሌ 24 1956 ከታተመው
ከዘመን ጋዜጣ የተወሰደ



በቀደመው ዘመን በዘመናዊ እቅድ
የተሰራው አዲስ ሕንፃ



የቀድሞ አዲሱ ፍልውሃ ሆቴል
የውስጠኛው ክፍል በከፊል



አሁን አዲሱ ፍልውሃ ሆቴል
የውስጠኛው ክፍል በከፊል

የአዲስ አበባ ፍልውሃ የተገኘበትንና በጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገበትን ትክክለኛ ዘመን ለመለየት ባይታወቅ ከዛሬ 1924 ዓመታት በፊት በንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በአንኮላላ ይገኝ የነበረው ቴለፌበር የተባላ አንድ የፈረንሳዊ ሊቅ ‹‹ ቦያዥ አቢሲኒ›› (የአበሻ አገር ጉዞ) በሚል የድርሰት አርእስት ተነስቶ በፃፈው መፅሐፍ ላይ ስለ ፍልውሃው ሁኔታ ሲናገር ‹‹ ንጉሡ ከአንኮለላ ቤተ መንግስት መኳንቶቻቸውን አስከትለው ቀድሞ ፊንፊኔ ከሚባለው የአሁኑ ፍልውሃ እንደደረሱ ሰፈር ሆነና ፣ከዚያ ድንጋያማ



ከሆነው መሬት ከሚፈልቀው የተፈጥሮ ሙቅ ውሃ መካንንቱ ከውሃው በመታጠብና በመጠጣት ተጠቀሙበት ።

የዚህ ቀበሌ መሬት በሙቅ ውሃው ምክንያት በጣም ረግረግ ስለሆነ በእግር በማለፍ አስቸጋሪ ነበር። ንጉሡም ከዕለታት አንድ ቀን ሲናገሩ ፡፡ አንቺ አሁን በዚህ ውስጥ የምትገኝ ቦታ የልጅ ልጆቼ ቤት ሰርተው ከተማ ያደርጉሻል የሚል ቃል እንደተናገሩ ደራሲው ገልፀዋል።

እንዲሁም ደግሞ ኖርኦስተር የተባለው ፀሐፊ ሲዘራኸርዖን አዲስ አበባ በሚል መፅሐፍ ሲያወሳ ፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ ከተማቸውን በ1875 ዓ.ም እንጦጦ ፣በኋላም አዲስ አበባ ላይ ከተማቸውን ሲቆረቁሩ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ መሣፍንቱና መኳንንቱ አዘውትረው ወደ ጠበሉ ቦታ ይመጡ እንደነበር ያስረዳል፡፡ከዚህም ሌላ በጹሑፍ እይውን እንደ ከአንዳንድ አረጋውያን ሽማግሌዎች እንደሚነገረው አዲስ አበባ ከተማ ለመሆን ያበቃት ምክንያት አንዱ የፍልውሃው መኖር ነው ይላል፡፡

ከዚህ ወዲህ በ1814 ዓ.ም ገደማ በቦታው ላይ ሁለት ክፍል ተሰርተው በአንደኛው ክፍል አንድ የብር አላድ በሁለተኛው ክፍል አንድ የብር መሐለት እየተከፈለበት ከአምስት በማይበልጡ ሠራተኞች ሥራውን ጀመረ፡፡

እንደከተማው መስፋፋትና እንደ ሕዝቡ ብዛት መጠን እንዲያደራጅ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን ሥራው እንዲሻሻል አዛዥ ወርቅነህንና ሌሎችንም ባለስልጣኖች የፍልውሃው ሥራ እንዲስፋፋ አዘው አሁን ወቅት ድረስ በመጠኑም ቢሆን አገልግሎቱን አበርክቷል፡፡

ከግማሽ ሚሊዮን ያለነሰ ህዝብ የሚኖርበት መናገሻ ከተማችን እንደ ዕድገቱ መጠን ማገኛውም አስፈላጊ ድርጅት እንዲኖረው ከሚታሰበው ፕሮገሬ አንዱ የሰውነት ንፅሕና መስጫ የሆነው የፍልውሃ የሥራ ጥናት እንዲሰራ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ፣ አዲስ እቅድ ተሰርቶ ያለቀው ፍልውሃው ለአድሚኒስትሬሽን ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን መደብር ቡና ቤት 80 ሰዎችን የሚይዝ ምሳ ቤት ለወንድና ለሴቶች ፀጉር ማስተካከያ ፣በሐኪም ትዕዛዝ ለሚጠመቁ ሕሙማን ማረፊያ የሚሆን የ6 ቤተሰብ መኖሪያ ክፍል ሲኖረው 18 ለአንደኛ ማዕረግ 56 ለሁለተኛ ማዕረግ ከነማረፊያ ቤቱ 15 ለሦስተኛ ማዕረግ የተደራጁ ክፍሎች ያላቸው ሲሆን በተጨማሪም በአንድ ጊዜ እስከ 30 ሰዎች ሊጠቀሙበት የሚችል አንድ የመዋኛ ክፍል ይገኝበታል፡፡ እንዲሁም በአሸንዳ መታጠብን ለሚፈልጉ በደንብ የተዘጋጀ ልዩ መታጠቢያ እንዳለው ይታወቃል፡፡

1956 ታትሞ ከወጣው ከመነን መፅሔት የተወሰደ

## የተረጋጋ ህይወት ለመኖር

መፅሐፍ አንብብ

ጠብ አታውራ (ማውራት ሲኖርብህ ግን ዝም አትበል)

ምክርና አስተያየት ለመቀበል አትፍራ

ለተደረገልህ ጥሩ ነገር አመስግን

አዳዲስ ቦታዎች ሂድ

በቂ እንቅልፍ ተኛ

የማታውቀውን ጠይቅ

ከየወሩ ገቢህ ላይ ቆጥብ ትንሽም ብትሆን

ፊተኛ ላይ የተናገርከትን እንዳትረሳ

ካነበብኩት ከብርቱካን ታደሰ

## አለቀለት ያሉት

ከጅረት አጠገብ ቆሞ የኖረ ዛፍ መብረቅ ገንደሰው

አሁን ድልድይ ሁኖ ያሸጋግራል ሰው

አለቀለት ያሉት ተልኮው መቼ አልቆ

ቆሞ የጠቀመ መሳ አያጣም ወድቆ፡፡

ካነበብኩ ከሪፖርተር ጋዜጣ
በእውቀቱ ሥዩም
ከአወት ክፍሉ

ጊምህ የከለላት
ድምፅህ ያስለላት
ክብርህ የደበቃት
ከበባህ ያነቃት
ቢቻላት የምትነፍስ
ብትፈልግ የምትፈስ
አለች ትንሽ ነፍስ

ስሱ ገላ
ቅዕበት ተድላ
ኩርፊያ አይጣል
ለምቦጭ መጣል
የምትፈለግ
የምወዳት
የደብቅኳት
የናፈቅኳት
ባንተ ውስጥ እኔን የማይባት
ትንሽዬ ነፍስ አለችኝ፡

ከትዝታ ጌታቸው

# የሞባይል ባንኪንግ ደህንነት፡ ገንዘብዎን ከአጭበርባሪዎች ለመጠበቅ ወሳኝ መመሪያዎች



የሞባይል ባንኪንግን ደህንነት በተጠበቀ ሁኔታ ለመጠቀምና ከማጭበርበር ወንጀለኞች ራስን ለመከላከል የሚከተሉትን ዋና ዋና እርምጃዎች መተግበር ያስፈልጋል፡

የይለፍ ቃል ጥንቃቄ፡ እንደ ስልክ ቁጥር ወይም የልደት ቀን ያሉ በቀላሉ የሚገመቱ የይለፍ ቃላትን አይጠቀሙ። የሚስጥር ቁጥርዎን ለማንም ሰው (ለቤተሰብም ቢሆን) አሳልፈው አይስጡ። ባንኮች ሚስጥራዊ ቁጥርዎን በስልክ እንደማይጠይቁዎት ያስታውሱ።

የOTP ኮድ ጥበቃ፡ ወደ ስልክዎ በSMS የሚላክ የማረጋገጫ ኮድ (OTP) "ገንዘብዎ" እንደሆነ ይቁጠሩት። ይህንን ኮድ ለባንክ ሰራተኛም ቢሆን በፍጹም አያጋሩ።

ሊንኮችን እና መተግበሪያዎችን መለየት፡ ስለ ሽልማት ወይም ስለ ሂሳብ መታገድ የሚመጡ አጠራጣሪ መልዕክቶችን እና ሊንኮችን አይክፈቱ። የባንክ መተግበሪያዎችን (Apps) ከትክክለኛዎቹ መተግበሪያ መደብሮች (Play Store/App Store) ብቻ ያውርዱ እና በየጊዜው ያዘምኑ።

የኢንተርኔት እና የስልክ ደህንነት፡ የባንክ አገልግሎት ሲጠቀሙ የራስዎን ዳታ እንጂ የህዝብ ነፃ Wi-Fi አይጠቀሙ። ሁልጊዜ ስልክዎን በቁልፍ (Lock) ይጠብቁ፣ እንዲሁም የባንክ ስራዎን ሲጨርሱ ከመተግበሪያው መውጣትዎን (Log out) ያረጋግጡ።

አስቸኳይ እርምጃዎች፡ ስልክዎ ቢጠፋ ወይም አጠራጣሪ የገንዘብ ዝውውር ቢመለከቱ፣ ሳይዘገዩ ለባንክዎ እና ለቴሌኮም አገልግሎት ሰጪዎ (ኢትዮ ቴሌኮም/ሳፋሪኮም) በመደወል ሂሳብዎና ሲም ካርድዎ እንዲታገድ ያድርጉ።

ከወ/ሮ መንበረ ሀድሉ

# ማውጫ


የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት ................................ 3

የድርጅቱ ስራ አመራር ቦርድ አባላት ................................ 5

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ................................ 6

የድርጅቱ ማኔጅመንት አባላት ........... 8

የፍ/አገ/ድ/ የሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር መልዕክት ................................ 9

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት አመሰራረት በአጭሩ ................................10

ከኢንፎርሜሽን ኮሙ/ቴክኖ/ ዳይሬክቶሬት................................ 13

የ2017 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ................................ 17-23

የድርጅታችን የላውንደሪ አገልግሎት እንደሚሰጥ ያውቃሉ? ..................... 24

የመዝናኛ እና የቁም ነገር አምድ ................................ 27-29

ከፎቶ ማህደር ........................... 32-33

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት የፋይናንስ መረጃ ........................... 34-45

ከፎቶ ማህደር ........................... 47-51

ድርጅቱን አገልግለው ጡረታ የወጡ ሰራተኞች ........................... 55


# የአዘጋጁ መልዕክት

ድርጅታችን በ2017 በጀት ዓመት ያስቀመጣቸውን የሽያጭ እና የትርፍ ሰቅድ ከማሳካት የተከያዩ የማርኬቲንግ እና የቢዝነስ ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም ከፍተኛ የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት ልዩ ልዩ ጊዜ የሚያሥገኙ ሥራዎች በመሰራታቸው እንዲሁም በድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ እና ማኔጅመንት በተሰሩ ስትራቴጂክ ጉዳዮች በበጀት ዓመቱ የያዘውን ሰቅድ በተሳካ ሁኔታ መፈፀም ችሏል።

የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ፣ ማኔጅመንት እና ሠራተኛ ማህበሩ ከመላው ሠራተኛ ጋር ከምንግዜውም በተሻለ ሁኔታ ተናቦና ተግባብቶ በመሥራቱ ከዚህ ውጤት መሳካት የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥቷል።

የ2017 በጀት ዓመት የድርጅቱን ሥራ አፈፃፀም አስመልክቶ በተዘጋጀው በዚህ መፅሔት ላይ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ፣ የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ፣ የሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ያስተላለፉትን መልዕክት እና የበጀት ዓመቱን የሥራ አፈፃፀም ፣ ኦዲት የተደረገ የሂሳብ ሪፖርት ፣ ያለፉትን አምስት ዓመታት የትርፍና የሽያጭ እንዲሁም የእንግዳ ቁጥር አፈፃፀም ፣ የድርጅቱን እንቅስቃሴ ገላጭ የሆኑ ፎቶግራፎች ፣ ጠቃሚ መረጃዎችን የያዙ መጣጥፎች እና የተለያዩ መልዕክቶችን የሚያስተላልፉ ግጥሞችን ያካተተ መፅሔት ከማዘጋጀት ጥረት ተደርጓል።


መልካም ንባብ

አዘጋጅ የገ/ጥ/አገ/ልማ/ኮሚ/
ዳይሬክቶሬት

## ትርፍ ክንውን አፈጻጸም

በበጀቱ በ2017 ዓ.ም ባሉት የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ጠቅላላ 80,569,326.00 ትርፍ ለማስተናገድ የታቀደ ሲሆን 82,758,078.00 ዓመታዊ ትርፍ ከታክስ በፊት የእቅዱን 102.72% አስናውኗል።

| የአፈጻጸም አይነት | እቅድ | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| ትርፍ | 80,569,326.00 | 82,758,078.00 | 102.72 |





በ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት ድርጅቱ ባሉት ዓላማ አስፈጻሚ የሥራ ሂደቶች አማካኝነት የተከናወኑ የእቅድ ክንውን አፈጻጸሞች በተናጠል ሲታዩ

## በተፈጥሮ ፈ/ስ/መዝናኛ ዋና የሥራ ሂደት

በዚህ ዓላማ አስፈጻሚ የሥራ ሂደት የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሲሆን የአገልግሎት አይነቶቹም በተመለከተ የመታጠቢያ አገልግሎት፣የሟውና ባዝ አገልግሎት፣የመታሻ አገልግሎት፣የእስቲም ባዝ አገልግሎት እና የክሊኒክ ህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ። በአጠቃላይ በእነዚህ የአገልግሎት መስጫዎች በ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት 241,649,659.00 የአገልግሎት ሽያጭ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 233,058,635.00 የሽያጭ ገቢ በማግኘት የእቅዱን 96.44% ተከናውኗል።


| | ዕቅድ | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| የመታጠቢያ ገቢ | 133,177,799.00 | 129,381,286.00 | 97.15% |
| የመታሻ ገቢ | 50,729,269.00 | 52,075,764.00 | 102.65% |
| የሟውና ባዝ ኖርማል እና ስፔሻል | 27,370,150.00 | 21,958,816.00 | 80.23% |
| የስቲም ባዝ ኖርማል እና ስፔሻል | 30,372,441.00 | 29,642,769.00 | 97.60% |
| ድምር | 241,649,659.00 | 233,058,635.00 | 96.44% |




## በሆቴል እና መዝናኛ አገልግሎት

የድርጅቱ ዓላማ አስፈፃሚ የሥራ ሂደት ሲሆን ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከምግብ፣ከመጠጥ፣ከመኝታ ኪራይ እና ከካፍቴሪያ አገልግሎት በ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት ብር 99,445,888.00 የሽያጭ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ ብር 103,515,087.00 ገቢ በማግኘት የእቅዱን 104.09% ተከናውኗል፡፡

| | የአገልግሎት አይነት | ዕቅድ | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ምግብ ሽያጭ | 71,617,500.00 | 71,964,594.00 | 100.48% |
| 2 | መኝታ ክፍል | 8,189,783.00 | 10,767,634.00 | 131.48% |
| 3 | መጠጥ | 11,898,950.00 | 14,332,193.00 | 120.45% |
| 4 | ካፊቴሪያ | 5,575,998.00 | 5,166,209.00 | 92.65% |
| 5 | ዳቦ ሽያጭ | 2,134,662.00 | 1,284,457.00 | 60.17% |
| | ድምር | 99,445,888.00 | 103,515,087.00 | 104.09% |



በ2017 ዓ.ም ...

| | ዕቅድ | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| የሱቅ ኪራይ ገቢ | 4,129,931.00 | 4,566,340.00 | 110.57 |
| ባር | 5,500,000.00 | 5,584,966.00 | 101.54 |
| ፓርኪንግ አገል | 9,125,000.00 | 8,436,791.00 | 92.46 |
| ልዩ ልዩ ገቢ | 500,000.00 | 1,099,164.00 | 219.83 |
| ድምር | 19,254,931.00 | 19,687,261.00 | 102.25 |


ልዩ ልዩ ገቢዎች




## በ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት በድርጅት ደረጃ ሽያጭ አፈፃፀም

| የአገልግሎት አይነት | በዕቅድ | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| ፍልውሃ እና ፊውስ ሰፈ | 241,649,659.00 | 233,058,635.00 | 96.44 |
| በሆቴልና መዝናኛ አገልግሎት ገቢ | 99,445,888.00 | 103,515,087.00 | 104.09 |
| ልዩ ልዩ ገቢ | 19,254,931.00 | 19,687,261.00 | 102.25 |
| አጠቃላይ አፈፃፀም | 360,350,478.00 | 356,260,983.00 | 98.87 |

የ2017 ዓ.ም በጀት አመት በድርጅት ደረጃ አፈፃፀም




በእንግዳ ቁጥር

**በፍልውሃ ፊውስ ሰዉ ዳይሬክቶሬት** ፡- ባሉት የአገልግሎት መስጫ ክፍሎ 2017 ዓ.ም በጀት ዓመት ውስጥ ይስተናገዳሉ ተብሎ የታቀደው ተገልጋዮች ቁጥር 2,023,310 እንግዶች ሲሆን ክንውኑ 1,591,415 ወይም 79% ለሚሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎት ተሰጥቷል

| | እቅድ | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| መታጠቢያ | 1,680,223 | 1,314,141 | 78 |
| መታሻ | 138,209 | 118,367 | 86 |
| ሳውና ባዝ | 104,574 | 76,128 | 73 |
| እስቲም ባዝ | 100,304 | 82,779 | 83 |
| ድምር | 2,023,310 | 1,591,415 | 79 |

## በሆቴል እና መዝናኛ አገልግሎት

የሆቴል መዝናኛ የ2017 በጀት በአመቱ ውስጥ ይስተናገዳሉ ተብሎ የታቀደው ተገልጋዮች ቁጥር 301,538 ሲሆን ክንውኑ 271,369 እንግዶች ወይም 90% ለሚሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎት ተሰጥቷል።

በመኝታ ክፍል ኪራይ፡- 2016 በጀት ዓመት ይስተናገዳሉ ተብሎ ይታቀደው ተገልጋዮች ቁጥር 14,022 ክንውኑ 14,744 ሲሆን ክንውኑ 105% ለሚሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎት ተሰጥቷል።

| | በጀት | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| ምግብ | 287,516 | 256,625 | 89 |
| መኝታ | 14,022 | 14,744 | 105 |
| ድምር | 301,538 | 271,369 | 90 |





በአጠቃላይ ከ2013 ዓ.ም እስከ 2017 ዓ.ም የተገኘውን የስያጭ የትርፍ እና

[illegible] በተመለከተ የ5 ዓመቱ አፈጻጸም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀ[illegible]


የሽያጭ አፈጻጸምን ከ2013 ዓ.ም እስከ 2017 ዓ.ም በተመለከተ

| | ዕቅድ | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| 2013 | 94,377,452.00 | 84,981,417.00 | 90.04 |
| 2014 | 177,889,405.00 | 171,263,675.00 | 96.28 |
| 2015 | 206,569,390.00 | 231,281,471.00 | 111.96 |
| 2016 | 321,231,398.00 | 304,291,426.00 | 94.73 |
| 2017 | 360,321,552.00 | 356,260,983.00 | 98.87 |





የትርፍ እቅድ ክንውን ከ2013 እስከ 2017 ዓ.ም በተመለከተ

| | በጀት | ክንውን | በ% |
|---|---|---|---|
| 2013 | 16,853,731.00 | 15,671,016.00 | 92.98 |
| 2014 | 27,159,378.00 | 24,344,340.00 | 89.64 |
| 2015 | 31,316,290.00 | 33,947,126.00 | 108.40 |
| 2016 | 61,481,506.00 | 69,533,616.00 | 113.10 |
| 2017 | 80,569,326.00 | 82,758,078.00 | 102.72 |



| | ዕቅድ | ክንውን | % |
|---|---|---|---|
| 2013 | 1,941,200 | 1,719,271 | 88.57 |
| 2014 | 2,291,026 | 1,895,095 | 82.72 |
| 2015 | 2,219,162 | 2,137,545 | 96.32 |
| 2016 | 2,386,565 | 2,003,547 | 83.95 |
| 2017 | 2,324,848 | 1,862,784 | 80.12 |



# የድርጅታችን የላውንደሪ አገልግሎት እንደሚሰጥ ያውቃሉ?

የፍልዉሃ አገልግሎት ድርጅት ለህብረተሰቡ የመታጠቢያ፣ የፊዚዮቴራፒ፣ የሳዉና ባዝ፣ የስቲም ባዝ እና የሆቴል አገልግሎት ይሰጣል።



ድርጅታችን ለነዚህ አገልግሎቶች ጥራቱና ንፅህናዉን የጠበቀ የላዉንደሪ ንፅህና መስጫ ክፍል ሲኖረዉ በተደራጀ ሠራተኞች ይህን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

የድርጅታች የጀርባ አጥንት የሆነዉ የላዉንደሪ ክፍላችን ከሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች መካከል በመታጠቢያ፣ በሳዉና ባዝ፣ በስቲም ባዝና በመታሻ ክፍሎች አገልግሎት ለመጠቀም በቀን ዉስጥ ከሚመጡ ከ7000 (ሰባት ሺ) በላይ እንግዶችን ለማስተናገድ ድርጅታችን ባለው 3 ማጠቢያ ማሽን ባለ60 ኪ.ግ፣1ማጠቢያ ማሽን ባለ 30 ኪ.ግ፣ 4 ማድረቂያ ማሽን ባለ 60 ኪ.ግ፣1 የአንሶላ መተኮሻ እና 1 ሲንጀር ማሽን የልብስ መስፊያ በመታገዝ ጥራቱን በጠበቀ አሰራር ፎጣና አንሶላ አጥቦና አድርቆ እያቀረበ ይገኛል።

ድርጅቱ ለሚሰጣቸዉ ለሆቴል አገልግሎት የሚዉል የመኝታ ክፍሎች አንሶላ፣ አልጋ ልብስ፣ ብርድ ልብስ፣ ፎጣ፣ የገበታ ጨርቅ፣ መጋረጃ፣ ለድርጅቱ ሰራተኞች በሙሉ የደንብ ልብስ ወይም ዩኒፎርም የእጥበት፣ የስፌትና ተኩስ ስራ እያከናወነ የሚገኝ ክፍል ነዉ።

ድርጅታችን ለደንበኞቻችን ንጽህናዉን የጠበቀ ፎጣና የአንሶላ አቅርቦት በሰዓት በጊዜዉ እናቀርባለን። ይህን አቅርቦት ስናቀርብ እንዲሁም በሆቴሉ አልጋ ለሚይዙ እንግዶች የልብስ እጥበትና ተኩስ ስራ በመስራ ለድርጅቱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሆኖ ይገኛል። ድርጅታችን ለ16 ሰዓት አገልግሎት ስለሚሰጥ ላዉንደሪም ክፍሉም ለ16 ሰዓት ያለማቋረጥ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

ለበዓል ዋዜማ፣ የሆቴል ግብዣዎችና የሰርግ ወራቶች ላይ የ24 ሰዓት አገልግሎት ይሰጣል።

የላዉንደሪ ክፍል ንቁና ታታሪ ሠራተኞችን በመያዝ ወደ ፊት ከዚህ በበለጠ ተደራጅቶ አገልግሎት ለደንበኞች ለመስጠት ተግቶ ለመስራት ዝግጁ ነዉ። በቀጣይም የዉስጥና የውጭ ደንበኞችን አስተያየት በመቀበል አገልግሎታችን ይበልጥ በማሳደግ የደንበኞቻችን ፍላጎት ለማርካት የበለጠ ጠንክረን እንደምንሰራ በቁርጠኝነት እናገራለሁ።


ሰብለ ገዛኸኝ
የላውንደሪ ሂ/ቡድን መሪ

## በድርጅታችን የማኔጀመንት አባላትና ሠራተኞች የሴቶች ሩጫ ተሳትፎ










# በድርጅታችን የማኔጀመንት አባላትና ሠራተኞች የታላቁ ሩጫ ተሳትፎ











# የመዝናኛ እና የቁም ነገር አምድ

## ፊንፊኔ፣ ፍልውሃ

ደካም ሲጫጫነኝ፣ ሰውነቴ ዝሎ፣
ስላም የሚሰጠኝ፣ ደካሜን መንግሎ፣
ከላዩ ላይ ጥሎ።
የፍልውሃው በበል፣ የፍልውሃው ውሃ፣
ጥንቆቲን አጥፍቶ፣ የሚሰጠኝ ፍሰሃ።
በተፈጥሮ ውሃ፣ በተፈጥሮ ገላት፣
ለስንቱ በሽታ፣ መፍትሄ ተገኝበት።
የጆርባ ህመም ነሽ፣ የወገብ ነሽ የገር፣
ፍልውሃ እያለ፣ ደሞ የምን ችግር?
ተፈውሶ ይሄዳል፣ ከበሽታው ደና፣
ውጋት ቁርጥማቱ፣ ከላዩ ላይ በና፣
እንደ ጤዛ ተና።
ደሞም ክፍ ካለ፣ ከበዛ ህመሞ፣
ያስታዋት ቦታ፣ በማሳጅ ታክሞ፣
ከበሽታ ድነው፣ ይሄዳሉ ደሞ።
ልምድ ባካበቱ፣ ማሳጅስቶቻችን፣
ፍቱን በሆኑ፣ ፈዋሽ እጆቻችን፣
ተደስተው ይሄዳሉ፣ በአገልግሎታችን።

## ሴላም አለ...

ደሞም እንደ እቃ፣ መሸመት ካማርት፣
ካሉን ሱቆች መሃል፣ መርጠው ደስ እንዳሉት፣
መሸመት ነው በቃ፣ እንደ ፍላጎትት።

## ምን ይሄ ብቻ...

ምናልባት ካማርት፣ የጣፈጠ ምግብ፣
እጅግ የሚያጎጉ፣ ሲያዩት ስመመገብ፣
ከፊንፊኔ ሆቴል፣ ምን ጠፍቶ በእውነቱ?
ይቀርብሎታል፣ ምግብ በያይነቱ።
የፃም ቢሉ የፍስክ፣ ያሻዎትን ሁሉ፣
ከፊንፊኔ ሆቴል፣ "አጣሁ" ያሉም የሉ

## ደሞ ሴላ...

በተንጣለለው፣ አዳራሾቻችን፣
በተዋበ ምንቱ፣ ወንበሮቻችን፣
ስብሰባ ካለ፣ ብሉም ለኮንፍረንስ፣
አዳራሽ አለሉት፣ የልቦን የሚያደርስ።
ወይ ልጆን ከዳሩ፣ ወይም ሳገባ ካለ፣
አዳራሾቻችን፣ ለዚህም ይሆናሉ፣
በባ በተዋበ፣ አዳራሾቻችን፣
ልምድ ባካበቱ፣ እንቁ ልጆቻችን፣
የማይደረሉትን፣ የሰርጉን ትዝታ፣
እኛ ጋር ያኑሩ፣ በታላቅ ደስታ።

## ሚስጥር...

ትልቅ እንድ ሚስጥር፣ ልንገርት ደፍሬ፣
ስለ አዳራሻችን፣ እንድ ሁለት ጨምሬ፣
"ሃይሉጋ" ተብሎ፣ በፊንፊኔ አዳራሽ የተጋቡ ሁሉ፣
እስካሁን ድረስ፣ የተፋቱም የሉ፣
ሞት እንኳን አይችልም፣ ሲነጣጥላቸው፣
በፊንፊኔ ሆቴል፣ ሲሆን ጋብቻቸው።
ከፊንፊኔ ሆቴል፣ ከፍልውሃ አዳራሽ፣
እኛ ጋር ፈልገው፣ አያጡም በጥራሽ።
ከሉቅ ከፍልውሃ፣ ከውብ ሆቴላችን፣
ፍቱን ከሆኑ፣ ማሳጅስቶቻችን፣
ስታንዳርድ ካላቸው፣ አዳራሾቻችን፣
ተደስተው ይሄዱ፣ በአገልግሎታችን።
ከእሁድ እስከ እሁድ፣ እኛ ጋር ምን ጠፍቶ?
መሄድ ብቻ ነው፣ ሰውነት አክሞ ነፍስን አስደስቶ!

ገጣሚ፡- የአሉላ እናት (ኢየሩሳሌም ብርሃኑ)

# የንስር አሞራ ሚስጥራዊ ተፈጥሮ



ፍጥረታት ሁሉ ይችን ምድር ሲወርሱ የተሰጣቸው ልዩ ውብ ተፈጥሮ አላቸው። ከነዚህ አስገራሚና ልዩ ውብ ተፈጥሮ አላቸው። ከነዚህ አስገራሚና ከተሰጣቸው ድንቅ የምድራችን የተፈጥሮ ፀጋ ከተሰጣቸው ፍጥረታት መካከል አንዱ የንስር አሞራ ነው። የንስር አሞራ ምድቡ ከአእዋፍ ወገን ሲሆን ተፈጥሮ የሰጠችው ድንቅ ሚስጥራዊ ተፈጥሮ ግን የተለየ ያደርገዋል።

ፎቶ:ከኢንተርኔት

ዛሬ በዓለማችን የሰው ልጆች አማካኝ የዕድሜ ጣሪያ 65 ዓመት በሆነበት ዘመን ንስር አሞራ ከአዕዋፋት ዘር 70 ዓመት የመኖር ፀጋ ተፈጥሮ የቸረችው የእድሜ ባለጸጋ ነው። አስገራሚው ነገር ይህ ድንቅ አእዋፍ ዕድሜው 40 ሲሆን ተፈጥሮ ሁለት አማራጮችን በፊቱ ታቀርብለታለች፤ እንደ አማረበት መሞት ወይም እድሜውን ወደ 70 አመት ከፍ ለማድረግ ተፈጥሮ ያዘጋጀችለትን የመከራና የስቃይ ጽዋ ምሬት አጣጥጦ በመጎንጨት ተጨማሪ የ30 ዓመት የድል ዋንጫ መቀዳጀት።

ንስር አሞራ ከተፈለፈለ ጀምሮ 40 ዓመት ከኖረ በኋላ ምግቡን ለማደን የሚገለገልበት ጥፍሮቹ ከመጠን በላይ ስለሚያድጉ ምግቡን መሬት ላይ ማንሳት ያቅተዋል። አጥንትን ሳይቀር መስበር አቅም ያለው መንቁሩ ስለሚታጠፍና ስለሚጣመም ምግቡን እንደወትሮው መመገብ ይሳነዋል። ክንፉና በአካሉ ላይ ያሉ ላባዎች ስለሚከብዱት፤ ያ ሰማየ ሰማያትን እየሰነጠቀ እንደ ሚግ ጀት ይበር የነበረው ሀይሉ ይከደዋል። በዚህ ወቅት ያ ድንቅ የአእዋፍ ዘር ንስር አሞራ በሁለት ዉሳኔዎች አጣብቂኝ ውስጥ ይወድቃል። የመጀመሪያው አማራጭ ከዚህ ካረጀ አካሉ ጋር ዝም ብሎ በመቀመጥ ሞቱን መጠበቅ፤ ወይም 5 ወር የሚፈጅ ስቃይና መከራ ያለበት መስዋእትነትን ከፍሎ ቀሪውን 30 አመቱን መውሰድ።



የንስር አሞራ ከቀረበለት ሁለት ምርጫዎች ቀሪ 30 ዓመቱን መቀጠል ከሆነ ምርጫው ተፈጥሮ ያዘጋጀችለትን የመከራ ጽዋ መጎንጨት ግድ ይለዋል፡ ፡ ይኸውም ከፍተኛ ተራራ ላይ በመዉጣት የብቻውን ጎጆ ቀልሶ ሱባኤ መግባት ይኖርበታል። በሱባኤውም ወቅት የመጀመርያ ስራዉ የአሩን መንቁር ከአለት ጋር በማጋጨት ነቅሎ መጣል ነው። ይህን ካደረገ በኋላ አዲስ መንቁር ያወጣለታል። መንቁሩ እስኪያድግ ድረስ ታግሶ በጎጆው ምንም አይነት ምግብ ሳይመገብ በፆም መቆየት ግዴታው ይሆናል።

የትዕግስቱ ፍሬ በሆነው በአዲሱ መንቁሩ የገዛ እግሩን አሮጌ ጥፍር ነቃቅሎ ይጥለዋል። አዲሱ የእግር ጥፍር ከበቀለለት በኋላ ደግሞ ይህንን አዲስ ጥፍር እንደመሳርያ በመጠቀም በሰዉነቱ የተጣበቁትን እንዳይበር እንቅፋት የሆኑትን የገዘፉና ያረጁ ላባዎችን ነቃቅሎ ይጥላል። በምትኩ አዲስ ላባ ያበቅላል። የሱባኤውን 5ወር በዚህ መልኩ በጀግንነት ከተወጣ በኋላ እንደገና ራሱን በራሱ ወልዶና ወጣት ሆኖ ወደ ንስሮች መንደር ብቅ ይላል። በእድሜው ላይ 30 አመት ጨምሮ በበረራው ሰማየ ሰማያትን እየሰነጠቀ ከፍ ብሎ እየበረረ ህይወትንና ደስታን በውሳኔው ባተረፈው 30 አመት ሙሉ በከፍታዎች ሁሉ ላይ በድል፣ በግርማና በሞገስ ይበራል። ከንስር ምን እንማራለን?

ከኢትዮጵያ አብርሃም

# አንዳንድ ሰዎች

አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ በስኬታችን በትዝብታችን ውስጥ እንኳን ስሜታቸውን የምንጠብቅላቸው፤ የምናከብርላቸው።

አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ ለነሱ ብንሆንና ሀቅ ቢኖረን እንኳን ለነሱ የምንሸነፍ፤ ከእኛ ይልቅ የእነሱን ስሜት የምንተብቅላቸው።

አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ በሕይወት ውስጥ የምንወዳቸው፤ የምናከብራቸው።

አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ እርግጠኝነት እንዲሰማን የሚያደርጉ፤ ለጥፋት ድርጊታቸው እንኳን ምክንያት የምንፈልግላቸው።

አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ ለነሱ ብለን ብዙ ነገር ካልንላቸው "ምን አገባኝ" ብለን የምንተውላቸው።

አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ እነሱን ላለማስቀየም ብዙ ነገር የምንታገስላቸው፤ "ችሎ" የምንችላቸው።

እነዚህ "አንዳንድ ሰዎች" ለዚህ ስሜታችሁ ግድ ሳይሰጣቸው ሲቀር፤ እናንተን ማስቀየም ግድ ሳይሰጣቸው ሲቀር፤ የእናንተን ምርጫና ሃሳብ ሳያከብሩ ሲቀሩ፤ የምታሳዩአቸውን ትህትናና ክብር ሲቆጥሩት ፤ ለትረዷቸው ሞክራችሁ ችላ ባላችሁት ጉዳዮች ላይ ልክ የሆኑ ሲመስላቸውና እናንተን ለመረዳት ቅንጣት ጥረት ሳያደርጉ ሲቀሩ... ትህትናህ እንደ ፍርሃት ፤ ትዕግስትህን እንደ አለማወቅ ፤ እና መስዋዕትነትህን እንደ ግዴታ ሲቆጥሩት ያለው ስሜት !

"አንዳንድ ሰዎች" ላንተ ያላቸውን ቦታ ባያከብሩትም፤ አንተ ግን ለራስህ ያለህን ክብር አሳልፈህ አትስጥ።

Setting Boundaries ለሰዎች ስትል የምትከፍለው መስዋዕትነት "ከማንነትህ" በላይ መሆን የለበትም። ትህትናህ ድንበር ካጣ ለሌሎች ሰዎች መረገጫ ይሆናል።

ዋጋህን ለማያውቁ ሰዎች ዋጋህን ለማስረዳት መሞከር ራሱ ሌላው የራስን ክብር አሳልፎ የመስጠት መንገድ ነው። ስለዚህ "ላንተ ያላቸውን ቦታ ባያከብሩትም" መተው የጥንካሬ ምልክት ነው።

ዋናው "ለራስህ ያለህን ክብር አሳልፈህ አትስጥ" ማለት የሌሎች ሰዎች ብልሹ ባህሪ አንተን ወደ እነሱ ደረጃ እንዲያወርድህ አትፍቀድ ማለት ነው!

ከትዝታ ጌታቸው

## መምህር እና ጊዜ

ጊዜ መምህር ነው፣
መምህር ጊዜ ነው፣
ፈተና ሕይወት ነው
ተማሪውም ሰው ነው
ሰውም ደካማ ነው፣
ደካማ ይወድቃል፣
ከወደቀም ወዲያ ክፉ ደጉን ያውቃል፣
ወድቆ የተነሳ ቁሞም የወደቀ፣
ከየት እንደሳተ ገብቶት ያላወቀ፣
ዳግመኛ ይወድቃል እየደጋገመ፣
የእግሩን ሥር መሬት ሳይወድ እየሳመ፣
አለመውደቅ ሳይሆን ከውድቀት መማር ነው፣
ሰውን ሰው የሚያደርገው።

የአደራ ሰማይ
የፍቅር ግጥሞች ስብስብ 2012
ከገጽ 57 የተወሰደ
ደራሲ ኪደን ማርያም/አጉማስ/ታደሰ
ካነበብኩት እቴነሽ ታደሰ

## በድርጅታችን አገልግሎት ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ስለ ማሳጅ (Massage) ሃይድሮቴራፒ (Hydrotherapy) አገልግሎት ጥቅም እና አጠቃቀም ምን ያህል ያውቃሉ?



የሃይድሮቴራፒ (Hydrotherapy) ወይም የውሃ ህክምና ማሳጅ በውሃ ግፊት ሙቀት እና ቅዝቃዜን በመጠቀም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የህክምና አይነት ነው። በተመሳሳይ ብቸኛው በፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ብቻ የሚሰጠው አገልግሎት በተፈጥሮ ፍልውሃ በመጠቀም የሃይድሮቴራፒ (Hydrotherapy) አገልግሎት በተጠቃሚ ደንበኞች ተወዳጅ እና ተፈላጊ በተለይ ለጡንቻ እና ለቦርጭ ለቁርጥማት፣ለመዝናናት እንዲሁም ለተለያዩ የጤና እክሎች መፍትሄነት ያገለግላል።

### ዋና ዋና ጥቅሞቹን በጥቂቱ እንደሚከተለው ለማየት ይቻላል፦

### 1. የጡንቻ ህመምን እና ውጥረትን መቀነስ

የሞቀ ውሃ ማሳጅ የደም ዝውውርን በማፋጠን በጡንቻዎች ውስጥ የተጠራቀሙ አላስፈላጊ ኬሚካሎችን (ለምሳሌ Lactic Acid) ያስወግዳል። ይህ ደግሞ፦

- የጡንቻ መኮማተርን (Cramps) ያቃልላል።
- ከከባድ ስፖርት በኋላ የሚመጣን የጡንቻ ህመም ይቀንሳል።
- የሰውነትን የመተጣጠፍ ብቃት ይጨምራል።

### 2. የአጥንት መገጣጠሚያ ህመምን ማስታገስ

እንደ አርትራይተስ (Arthritis) ያሉ የመገጣጠሚያ ህመም ላለባቸው ሰዎች ሃይድሮቴራፒ ፍቱን ነው።

- ውሃ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የሰውነት ክብደት ስለሚቀንስ በመገጣጠሚያዎች ላይ የሚኖር ጫና ይላላል።
- የመገጣጠሚያዎችን እንቅስቃሴ (Range of motion) ያሻሽላል።

### የአካል ብቃት ጥቅሞች

- የጡንቻ ህመምን ይቀንሳል፦ በስራ ወይም በስፖርት ምክንያት የጠነከሩና የደከሙ ጡንቻዎችን ለማዝናናት ይረዳል።
- የደም ዝውውርን ያሻሽላል፦ ደም በሰውነታችን ውስጥ በተገቢው ሁኔታ እንዲዘዋወር በማድረግ ለህዋሳት በቂ ኦክስጅንና ምግብ እንዲደርስ ያደርጋል።
- ተለዋዋጭነትን ይጨምራል፦ የመገጣጠሚያዎችና የጡንቻዎች የመለጠጥ አቅም እንዲጨምር በማድረግ እንቅስቃሴን ያቀልላል።
- የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅም ያጠናክራል፦ የነጭ የደም ሴሎችን በማነቃቃት በሽታን የመከላከል አቅምን ይጨምራል።

# ከኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የመጡ የበላይ ኃላፊዎች ድርጅታችንን ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት









# የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት የፋይናንስ መረጃ

**SPA SERVICE ENTERPRISE**
**STATEMENT OF PROFIT OR LOSS AND OTHER COMPREHENSIVE INCOME**
**FOR THE YEAR ENDED 30 JUNE 2025**

| | Notes | 2025 ETB | 2024 ETB |
|---|---|---|---|
| REVENUE | 5 | 335,002,255 | 296,131,426 |
| COST OF SALES | 7 | 180,648,903 | 151,805,191 |
| GROSS PROFIT | | 154,353,352 | 144,326,235 |
| Other income | | 21,128,727 | 8,225,614 |
| | | **175,482,078** | **152,551,849** |
| **EXPENSES** | | | |
| Impairment loss | 14 | 307,822 | 730,230 |
| Administration | 8 | 100,485,231 | 79,675,160 |
| Finance cost | 9 | 658,622 | 2,522,632 |
| | | 101,451,675 | 82,928,021 |
| **PROFIT BEFORE TAX** | | **74,030,403** | **69,623,828** |
| Income tax expense | 10.2 | (21,565,275) | (26,314,922) |
| **PROFIT FOR THE YEAR** | | **52,465,128** | **43,308,906** |
| **OTHER COMPREHENSIVE INCOME** | | - | - |
| **TOTAL COMPREHENSIVE INCOME** | | **52,465,128** | **43,308,906** |

## SPA SERVICE ENTERPRISE
## STATEMENT OF FINANCIAL POSITION
## AT 30 JUNE 2025

| | Notes | 2025 ETB | 2024 ETB |
|---|---|---|---|
| **ASSETS** | | | |
| **NON- CURRENT ASSETS** | | | |
| Property, plant and equipment | 12 | 198,757,430 | 184,508,016 |
| Right use of asset | 13 | 44,753,996 | 44,753,996 |
| Government bond | | 300,000 | 300,000 |
| Investment property | 18 | 1,095,165 | 1,156,008 |
| Intangible asset | 19 | 1,298,292 | 1,298,292 |
| | | 246,204,883 | 232,016,311 |
| **CURRENT ASSETS** | | | |
| Trade and other receivables | 14 | 41,314,181 | 42,483,881 |
| Inventory | 17 | 35,251,567 | 21,753,166 |
| Cash and bank balances | 15 | 18,469,206 | 9,196,300 |
| | | 95,034,953 | 73,433,346 |
| **TOTAL ASSETS** | | 341,239,836 | 305,449,657 |
| **EQUITY AND LIABILITIES** | | | |
| **CAPITAL AND RESERVES** | | | |
| Paid up capital | | 4,382,705 | 4,382,705 |
| Legal reserve | | 2,961,065 | 2,165,445 |
| Retained earning | | 171,926,681 | 152,293,213 |
| | | 179,270,451 | 158,841,363 |
| **NON- CURRENT LIABILITIES** | | | |
| Employee benefit-Long term | 21 | 4,940,775 | 4,077,574.14 |
| Deferred tax liability | 11.2 | 34,740,317 | 39,191,502 |
| Bank loan | 23 | 30,392,176 | 207,465 |
| | | 70,073,269 | 43,476,541 |
| **CURRENT LIABILITIES** | | | |
| Trade and other payables | 20 | 35,836,363 | 46,956,798 |
| Industrial development fund | 24 | 11,898,481 | 11,898,481 |
| State dividend payable | 25 | 5,701,426 | 10,819,375 |
| Other tax payable | 22 | 7,884,961 | 4,988,593 |
| Profit tax payable | 10.1 | 25,375,443 | 23,992,327 |
| Employee benefit-short term | 21 | 5,507,263 | 4,476,181 |
| | | 92,203,938 | 103,131,755 |
| **TOTAL LIABILITIES** | | 162,277,207 | 146,608,296 |
| **TOTAL EQUITY AND LIABILITIES** | | 341,547,658 | 305,449,659 |

5

## SPA SERVICE ENTERPRISE
## STATEMENT OF CHANGES IN EQUITY
## FOR THE YEAR ENDED 30 JUNE 2025

| | Paid up Capital ETB | Legal Reserve | Retained earning ETB | Total ETB |
|---|---|---|---|---|
| At 1 July 2023 | 4,382,705 | 795,620 | 138,107,235 | 143,285,560 |
| | | | | 0 |
| Profit for the year | - | - | 43,308,906 | 43,308,906 |
| Prior year adjustment | - | - | (26,957,483) | -26,957,483 |
| Transfer to legal reserve | - | 2,165,445 | (2,165,445) | - |
| At 30 June 2024 | 4,382,705 | 2,961,065 | 152,293,213 | 159,636,983 |
| At 1 July 2024 | 4,382,705 | 2,961,065 | 152,293,213 | 159,636,983 |
| Profit for the year | - | - | 52,465,128 | 52,465,128 |
| Prior year adjustment | - | - | (32,831,660) | (32,831,660) |
| Transfer to legal reserve | - | - | - | - |
| At 30 June 2025 | 4,382,705 | 2,961,065 | 171,926,681 | 179,270,451 |

## SPA SERVICE ENTERPRISE
## STATEMENT OF CASH FLOWS
## FOR THE YEAR ENDED 30 JUNE 2025

| | Note | 2025 ETB | 2024 ETB |
|---|---|---|---|
| **CASH FLOWS FROM OPERATING ACTIVITIES** | | | |
| Profit for the year before taxation | 5 | 74,030,403 | 69,623,828 |
| **Adjustments for:** | | | |
| Depreciation of property, plant and equipment | 12 | 16,619,157 | 14,142,866 |
| Impairment loss | 14 | (307,822) | |
| Prior period adjustment | | (32,036,040) | (26,957,483) |
| | | **58,305,698** | **56,809,211** |
| **Movements in working capital** | | | |
| (Increase)/decrease in inventory | 17 | (13,498,400) | (2,577,238) |
| (Increase)/decrease in trade and other receivables | 14 | 1,169,701 | (16,836,427) |
| Increase in trade and other payables | 20 | (11,120,435) | 3,148,681 |
| (Decrease)/increase in employee benefit | 10.1 | 1,894,284 | 1,130,917 |
| (Decrease)/increase in other taxes payable | 22 | 2,896,368 | 3,077,269 |
| **Cash generated from operations** | | **39,647,215** | **44,752,413** |
| Withholding tax paid | | (641,017) | (533,593) |
| Profit tax paid | 10.2 | (23,992,327) | (13,529,868) |
| **Net cash generated from operating activities** | | **15,013,871** | **30,688,952** |
| **CASH FLOWS FROM INVESTING ACTIVITIES** | | | |
| Property, plant and equipment | 12 | (45,025,668) | (34,310,252) |
| Addtion to Right of Use asset | | | (170,686) |
| Adjustment on Property, plant and equipment | | 14,217,944 | 602,397 |
| **Net cash used in investing activities** | | **(30,807,724)** | **(33,878,541)** |
| **CASH FLOWS FROM FINANCING ACTIVITIES** | | | |
| State dividend | | (5,117,949) | 9,914,141 |
| loan proceed/settlement | 23 | 30,184,712 | 220 |
| **Net cash used in financing activities** | | **25,066,763** | **9,914,361** |
| **Net increase in cash and cash equivalents** | | 9,272,906 | 6,724,772 |
| Cash and cash equivalents at 1 July 2023 | | 9,196,301 | 2,471,529 |
| **Cash and cash equivalents at 30 June 2024** | | **18,469,206** | **9,196,301** |
| Represented by: | | | |
| Bank and cash balances | 15 | 18,469,206 | 9,196,300 |
| | | **18,469,206** | **9,196,300** |

7

## SPA SERVICE ENTERPRISE
## NOTES TO THE FINANCIAL STATEMENTS
## FOR THE YEAR ENDED 30 JUNE 2025

5 **REVENUE**

| | 2025 ETB | 2024 ETB |
|---|---|---|
| Room service | 10,797,857 | 9,989,598 |
| Food ,cafeteria ,and beverages | 91,046,026 | 78,686,508 |
| Bath and shower | 127,675,454 | 112,143,335 |
| Therapy and sauna bath | 105,482,919 | 91,157,722 |
| | 335,002,255 | 291,977,164 |

6 **OTHER INCOME**

| | 2025 ETB | 2024 ETB |
|---|---|---|
| Bakery income | 1,284,457 | 1,880,534 |
| Laundry Income | 4,879 | 10,760 |
| Parking income | 8,436,791 | 3,296,859 |
| Shop rent | 7,790,207 | 4,154,262 |
| Other income | 3,612,394 | 3,037,470 |
| | 21,128,727 | 12,379,876 |

7 **COST OF SALES**

7.1 **COST OF MATERIALS AND SERVICES**

| | 2025 ETB | 2024 ETB |
|---|---|---|
| Food ,cafeteria and beverages | 41,933,407 | 39,182,507 |
| Bath and shower | 19,914,517 | 19,166,623 |
| Therapy and sauna bath | 1,262,410 | 1,585,429 |
| Water | 44,840,669 | 26,824,330 |
| Room service | - | - |
| Clinic | - | - |
| | 107,951,003 | 86,758,889 |

**OVERHEAD COST**

| | 2025 ETB | 2024 ETB |
|---|---|---|
| Salary and related | 56,394,421 | 50,819,205 |
| Repair & maintenances | - | - |
| Depreciation | 16,558,314 | 14,082,023 |
| Cleaning and sanitation | (70,836) | 90,595 |
| Other supplies | (183,998) | 54,478 |
| | 72,697,900 | 65,046,301 |
| **Total Cost of sales** | 180,648,903 | 151,805,191 |

## SPA SERVICE ENTERPRISE
## NOTES TO THE FINANCIAL STATEMENTS
## FOR THE YEAR ENDED 30 JUNE 2025

### 8 ADMINISTRATION

| | 2025 | 2024 |
|---|---|---|
| | ETB | ETB |
| Salary and related benefits | 49,566,668 | 40,300,719 |
| Travel and per diem | - | 45,630 |
| Stationery and printing | 1,656,403 | 1,612,877 |
| Fuel and lubricant | 7,057,333 | 5,303,635 |
| Electricity | 6,801,995 | 5,727,354 |
| Commission | 162,968 | 149,058 |
| Hotel | 390,491 | 459,232 |
| Repair and maintenance | 8,139,876 | 8,271,116 |
| License and registration | 11,991 | 8,232 |
| Cleaning and sanitation | 3,214,634 | 3,001,648 |
| Uniform and clothing | 2,936,977 | 341,881 |
| Transportation | 424,416 | 162,936 |
| Periodical | 29,628 | 193,031 |
| Membership fee | 112,556 | 17,500 |
| Insurance | 1,242,637 | 1,285,347 |
| Donation | 328,800 | 482,276 |
| Advertisement | 623,816 | 1,194,785 |
| Penalty | 439,951 | 1,222 |
| Legal and Professional fee | 1,095,874 | 387,183 |
| Communication | 688,564 | 536,406 |
| Entertainment | 2,901,322 | 1,903,802 |
| Board fee/management fee | 335,500 | 435,500 |
| Property tax | 2,596,806 | 2,485,264 |
| Electrical and other supply | 8,019,036 | 4,146,160 |
| Extra ordinary | 1,299,175 | - |
| Bank service charge | 14,352 | 21,409 |
| Miscellaneous | 701,284 | 1,105,400 |
| | **100,793,053** | **79,675,160** |

### 9 FINANCE COST

| | 2025 | 2024 |
|---|---|---|
| | ETB | ETB |
| Interest on bank loan | 658,622 | 2,522,632 |
| | **658,622** | **2,522,632** |



# የሀገርን እንወቅ ክበብ አባላት በጉብኝት ላይ

















# ድርጅቱን አገልግለው ጡረታ የወጡ ሰራተኞች



# በበጀት አመቱ ከዚህ አለም በሞት የተለዩን ሰራተኛ

## ልንረሳህ አልቻልንም

ቅን አሳቢው አእምሮህ....... ትሁት አንደበትህ
ሰው አፍቃሪ ልብህ ..................ግዙፍ ማንነትህ
ሁሌም እየመጣ ......... ወደ ልቦናችን
ልንረሳህ አልቻልንም ...... አሴ ወንድምችን
ሃላፊነት ወሳጅ .................ታታሪ ትልበትህ
ስራ ወዳድ ወኔህ .........ብርቱ ማንነትህ
ሁሌም እየመጣ ............ ወደ ልቦናችን
ልንረሳህ አልቻልንም.......... አሴ ወንድምችን
ሃቀኛ ለእውነት ተሟጋች .......ስብእናህ
ሁሉን በአንድ ተመልካች ......ትህትናህ
የስራ አፈጣጠም.......... ቅልጥፍናህ
ሁሌም እየመጣ ......ወደ ልቦናችን
ልንረሳህ አልቻልንም .....አሴ ወንድማችን
ወዳጅ ቤተሰቦችህን ......አፍቃሪ
የስራ ባልደረቦችህን ......አክባሪ
ለልጆችህ ከፍታ .... ታታሪ
የደግነት.... ፊትአውራሪ
መሆንህ ሁሌም እየመጣ ........ወደ ልቦናችን
ልንረሳህ አልቻልንም ............አሴ ወንድማችን

ከቤተሰቦቹ



አቶ አሰፋ ገ/ስላሴ



አሴ ሩቅ አሳቢ ሞትህ ድንገተኛ
አንተን አጥቶ መኖር ጭንቅ ነዉ ለኛ
ግድ ሆነብንና ቀርጦ መለያየት
ደሞ ትናፍቀናለህ ላይኖር መተያየት
አንተን ለማስታወስ አለን ብዙ ምክንያት
እንዳንተ መልካምነት እንደደግነትህ
ነፍስህን ይማረዉ ገነት ይሁን ቤትህ

ሰብለ ገዛኸኝ

## የምስጋና የምስክር ወረቀት

ለ፦ [illegible]

[illegible]

## Certificate of Appreciation

TO:- SPA Service Enterprise

It is with great respect that we give you this certificate of appreciation for strengthen our association and support for 20th years Graduation Anniversary of 33rd Regular Diploma Course Police Officers from Ethiopian Police University.

[illegible]

ቀን 25/5/2017
Date 02/02/2025

---

ከቁርቆስ ክፍለ ከተማ ትራፊክ ቁጥጥር ዲቪዚዮን

# የምስክር ወረቀት

ለ [illegible]

በቁርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ትራፊክ ቁጥጥር ዲቪዚዮን የ2017 የስራ አፈፃፀምን አስመልክቶ በተዘጋጀው የተሓድሶ ፕሮግራም ዝግጅት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ላደረጉልን የድጋፍ አስተዋፅኦ ከልብ እያመሰገንን ይህ የምስጋና የምስክር ወረቀት በአክብሮት ጋር ተሰጥትዎታል።

ያደሳ ሚደቅሳ

ኢ/ር

ትራፊክ ቁጥጥር ዲቪዚዮን ኃላፊ

ነሃሴ 2017 ዓ/ም አዲስ አበባ